150 ሚሊ ሜትር ዳያሜትር ስፋት ያላቸው ዋናዎቹ ቀዳዳዎች፣ ሞቃት አየር እንዲወጣ ለማድረግ በውጫዊው ግድግዳ ላይ ተበስተዋል። ማንኛውም ነገር ወደ አፓርታማዎ እንዳይገባ ለመከላከል የውጭ ሽፋን ተገጥሟል።

## ለእርሶ የገባነው ቃል፡-

እኛ እርስዎን ስንጎበኝ፣ ሁሌም፡-

- እርስዎን እና ቤትዎን እናከብራለን
- መታወቂያችንን እናሳይዎታለን
- ከእያንዳንዱ ጉብኝት በኋላ ያቆሸሽነውን ቦታ እናፀዳለን
- አዳዲስ ነገሮችን እንዲያውቁ እናደርጋለን



## ጥያቄ አልዎት?

1800 519 721 ወይም

HighRiseCooling@homes.vic.gov.au

ሲደውሉልን ወይም ኢሜይል ሲልኩልን፣ አንድ የቡድናችን አባል መልስ ይስጥዎታል።

ከኤሌክትሪክ ኃይል ክፍያዎችዎ ጋር በተያያዘ ለማገዝ ድጋፍ አለ። ስለ ኤሌክትሪክ ኃይል ዋጋ ቅናሾች በ **services.dffh.vic.gov.au/energy** በኩል ይወቁ

እንዲሁም፣ **sustainability.vic.gov.au** ን በመጎብኘት እና ‘Cool your home’ የሚለውን በመፈለግ ቤትዎን ለማቀዝቀዝ ጥቅማጥቅሞችን እና ምክሮችን ማግኘት ይችላሉ።

በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ፣ 1 Treasury Place, Melbourne. © State of Victoria፣ ሆምስ ቪክቶሪያ፣ መጋቢት 2025። (HV002625)። በFinsbury Green, Melbourne Victoria, 3000 የታተመ።

homes victoria

### ሰማይ-ጠቀስ ፎቆችን የማቀዝቀዝ ፕሮግራም

# ነፃ የአየር ሙቀት መመጠኛዎን ይውሰዱ



Amharic | አማርኛ

VICTORIA State Government

# የሰማይ-ጠቀስ ፎቆች ማቀዝቀዣ ፕሮግራም ምንድን ነው?

## በሞቃታማ የአየር ጠባይ ወቅት እርስዎን ለማቀዝቀዝ እና የበለጠ ምቹ ለማድረግ ነፃ የአየር ሙቀት መመጠኛ እያስገባን ነው።

እቃው እና መገጣጠሙ በነፃ እና እንደ ምርጫዎ ናቸው፣ በሚገጠምበት ጊዜም ከቤትዎ መውጣት አያስፈልግዎትም።

አዲሶቹ የአየር ሙቀት መመጠኛዎች:-

- ✓ ኃይል ቆጣቢ
- ✓ ድምጽ የሌለው
- ✓ በርቀት መቆጣጠሪያ ለማሰራት ቀላል
- ✓ በክፍሎች መካከል መንቀሳቀስ የሚችል *(ሙቅ አየር ወደ ውጭ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችል ዋና ቀዳዳ ካለ)*

በሞቀት የአየር ሁኔታ **በአየር ማቀዝቀዣ ቤትን ለማቀዝቀዝ በቀን 1 ዶላር ከ20 ሳንቲም** አካባቢ ያስከፍላል ተብሎ ይገመታል፣ ይህም የሚሆነው በቀን በአማካይ **ለ 4 ሰአታት እንደምንጠቀም**

# የአየር ማቀዝቀዣ ከፈለጉ

## 1. ቀጠሮ ይያዙ

ደብዳቤ ሲደረሰዎት፣ በሚከተሉት መንገዶች የአየር ማቀዝቀዣ እንደሚፈልጉ ያሳውቁን:-

- እቃዎች በሚታዩበት ትርኢት ላይ ከእኛ ጋር በመነጋገር
- ኢሜይል በማድረግ:- HighRiseCooling@homes.vic.gov.au
- ስልክ በመደወል:- 1800 519 721

## 2. የቅድመ ሥራ ፍተሻ

ቡድናችን በቤትዎ ውስጥ ያገኝዎታል። አዲሱን የአየር ማቀዝቀዣዎን የምንገጥምበትን ቦታ እንመረምራለን እና የመግጠሙን ሂደቱን እንገልፃለን።

## 3. ዋናዎቹን ቀዳዳዎች መብሳት - ይህ ለሁሉም ቤቶች አይደለም

ቀደም ሲል ዋናዎቹ ቀዳዳዎች ከሌሉዎት፣ ለአዲሱ የአየር ማቀዝቀዣዎ ግድግዳ ላይ ቀዳዳ መብሳት አለብን።

የአየር ሙቀት መመጠኛዎን ለማንቀሳቀስ በአፓርታማዎ ውስጥ አንድ ወይም ሁለት ቀዳዳዎች ይፈልጉ እንደሆነ መምረጥ ይችላሉ።

እንደጨረስን ቤትዎን አፅድተን እና ሁሉንም በገር በቦታው መልሰን እንወጣለን እና ቀዳዳውም ይሸፈናል።

## 4. የአየር ማቀዝቀዣ መትከል

ቡድናችን የአየር ማቀዝቀዣውን እንዴት እንደሚሰራ ያሳይዎታል እና እንዴት የበለጠ መጠቀም እንደሚችሉ አጭር መመሪያ ይሰጥዎታል።

በዚህ ሂደት ውስጥ ከቤትዎ መውጣት አያስፈልግዎትም።

## 5. የመጨረሻ ፍተሻ

አዲሱ ማቀዝቀዣ በትክክል እየሰራ መሆኑን በመፈተሽ እናረጋግጣለን እና ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን። የእርስዎን ይፋዊ አስተያየት ለመስማት ቀጣይ የዳሰሳ ጥናት እናደርጋለን።




አዲሱ የአየር ማቀዝቀዣዎ **DeLonghi Pinguino PAC EL112 CST** ነው